# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው
ያስነብቡ!
አባዝተው
ያሰራጩ!

ቁጥር 99 መጋቢት 30 2002 ዓ.ም

ምርጫን እንደመሰለያ መሳሪያ የሚጠቀመው ወያኔ በድህረ ምርጫ 97 በህዝባችን ላይ የፈጸመው አይነት ፋሽስታዊ ጭፍጨፋ እንዳይደገም ከተፈለገ ነጻ እና ገለልተኛ የሆነ የምርጫ አስፈጻሚ አካላት፤ ለሁሉም እኩል የሚያገለግል የሚዲያ አገልግሎት፤ ታማኝነታቸው ለህገመንግሥቱ ብቻ የሆነና ከፖለቲካ ወገናዊነት የጸዱ የፖሊስ፤ የመከላኪያና የደህንነት ተቋማት መመስረት ይኖርበታል።

ለወያኔ እድሜ መራዘሚያ ህጋዊና ሞራላዊ መሰረት እንዲያስገኝ ታስቦ በሚካሄድ ምርጫ መሳተፍ ለህዝባችን የሚያስገኘው ፋይዳ አይኖርም!!!

## የዘረኛውና አምባገኑ መለስ ዜናዊ አገዛዝ በአሜሪካ ድምጽ ራድዮ እና በሰብዓዊ መብት ተከራካሪ ድርጅቱ ሂውማን ራይትስ ዋች ላይ የተለያዩ ወቀሳዎችን መሰንዘሩን ቀጥሏል

ከተለያዩ አቅጣጫዎች ጫና እየደረሰበት ያለው የመለስ ዜናዊ አምባገነናዊ አገዛዝ፤ የግንቦት ወር በተቃረበ ቁጥር የባለስልጣናቱም ውጥረት እየገነፈለ መጥቷል። ከሰሞኑ ሂውማን ራይትስ ዋች በሚባለው የሰብአዊ መብት ድርጅት እና በአሜሪካ ድምጽ ራድዮ (ወይም ቪኦኤ) የአማርኛ ዝግጅት ክፍል ላይ ከመለስ ዜናዊ ጀምሮ የአገዛዙ ባለስልጣናት የሃሰተኛ ወቀሳዎች ናዳ ሲያወርዱ መሰንበታቸው በሰፊው ተዘግቧል።

መጋቢት 24 ቀን 2002 ዓም የበረከት ስምኦን ምክትል ሽመልስ ከማል ሂውማን ራይትስ ዋች እና ቪኦኤ ኢትዮጵያ ውስጥ ሊካሄድ ያለው ምርጫ ዴሞክራሲያዊ እንደማይሆን እና ለዴሞክራሲያዊ ምርጫ የሚያመቹ ሁኔታዎች እንደሌሉ ለማሳየት አሲረዋል ሲል ለጋዜጠኞች ገልጿል። መለስ ዜናዊ የቪኦኤ ስርጭቶች በኢትዮጵያ ውስጥ አለመረጋጋትን ለማስፈን እና ጥላቻን ለማስፋፋት የታለሙ ናቸው ባለ ጊዜ የአሜሪካ መንግስት "መሰረተ ቢስ ወቀሳ!" ብሎ ምላሽ መስጠቱን ከዚህ ቀደም መዘገባችን ይታወሳል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## የወያኔው አምባገነን አገዛዝ በንጹሃን ዜጎች ላይ እየፈጸመ ያለውን ግፍ ማስቆም የሁላችንም ግዴታ ነው ተባለ

ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ ባቋቋመው አሻንጉሊት ፍርድ ቤት አማካኝነት በኦሮሞ የፖለቲካ እስረኞች ላይ የሞትና እድሜ ልክ እስራት ፍርድ ማስፈረዱ የታወቀ ሲሆን ባለፈው ሳምንት ዋለ በተባለው የድራማ የፍርድ ሂደት የሞት ፍርድ የተፈረደበትን መስፍን አበበ አብዲሳና የእድሜ ልክ እስራት የተፈረደበትን ተስፋሁን ጨመዳ ጉርሜሳን ጨምሮ በአስራ ሁለት የፖለቲከኛ እስረኞች ላይ ከ10 ዓመታት በላይ በሚሆን እስር የተለመደውን የዘፈቀደ ፍርድ መስጠቱ በተለያዩ የመረጃ ድረገጾች ላይ ተገልጿል። ከነኚህ የፖለቲካ እስረኞች ውስጥ የሶስት ልጆች እናት የሆነችውና በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን በጋዜጠኝነት ታገለግል የነበረችው ወይዘሮ ሌሊሴ ወዳጆ እንደምትገኝበት ድረገጾቹ ጨምረው ገልጸዋል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ዜና በጋምቤላ ክልል የወያኔው አገዛዝ የታጠቁ ሃይሎች ዜጎችን የማዋከብ የማሰርና የመግደል ተግባር በከፋና በተባባሰ ሁኔታ መቀጠሉን አስመልክቶ የጋራ እንቅስቃሴ ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ በትናንትናው ዕለት ባወጣው ጽሁፍ አስታውቋል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## የወይዘሪት ብርትኳን ሚደቅሳ የጤና ሁኔታ አሳሳቢነት በሰፊው መዘገቡ ያደናገጠው ወያኔ የህሊና እስረኛዋ በቪዲዮ ተቀድታ በቴሌቪዥን እንድትታይ ማስደረጉ ታውቋል

ባለቤትነቱ የኢትዮጵያ ህዝብ የሆነውና ባሁኑ ሰዓት በወያኔ ቁጥጥር ስር የሚገኘው የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን አገልግሎት (ወይም ኢቲቪ) እሁድ እለት ባስተላለፈው ዝግጅት ወይዘሪት ብርትኳንን ማሳየቱ የጤንነታቸውን አሳሳቢነት ዜና ለማስተባበል የተደረገ ሙከራ ነው ተብሏል።

ኢቲቪ እሁድ እለት ባስተላለፈው ዝግጅት የ"ጀስቲስ ፎር ኦል ፕሪስን ፌሎውሺፕ" የተባለውንና በፓስተር ዳንኤል ገብረስላሴ የሚመራውን ግብረ ሰናይ ድርጅት ስራ መጎብኘት በሚል ከለላ ወይዘሪት ብርትኳንን ካሳየ በኋላ የወያኔ ደጋፊዎች ዝግጅቱን እያጣቀሱ የወይዘሪት ብርትኳንን መታመም ዜና ለማጣጣል ሲሞክሩ ታይተዋል። አንዳንድ አስተያየት ሰጪዎች፥ ቀድሞውኑ አሳሳቢ የሆነው የወ/ት ብርትኳን ስነ-ልቦናዊ ደህንነት ሆኖ ሳለ ውጫዊ አካሏን ማሳየት በቂ ማስተባበያ እንዳልሆነ ገልጸዋል።

የወይዘሪት ብርትኳን ስነ-ልቦናዊ ደህንነት አሳሳቢ ስለመሆኑ ባለፉት ጥቂት ሳምንታት የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ቢሮ ሪፖርትን እና የወይዘሪት ብርትኳንን አዛውንት እናት ጨምሮ በተለያዩ ምንጮች መዘገቡ ይታወሳል። የግንቦት 7 ድምጽ ባገኘው ተጨማሪ መረጃ መሰረትም፥ የአስታራቂ ሽማግሌዎች ተብዬው ቡድን አባል የሆነውና በቴለቪዥን ዝግጅቱ የድርጅቱን ስራ ሲያሳይ የነበረው ፓስተር ዳንኤል ራሱ የወ/ት ብርትኳን የጤና ሁኔታ አሳሳቢ መሆኑን ለሽማግሌዎቹ ቡድን ተናግሯል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## በህጋዊ እና ሰላማዊ ተቃዋሚ ፓርቲ አባላት ላይ የሚደርሰው እንግልት እና የመብት ረገጣ እየተባባሰ መሄዱ በአገዛዙ ዘንድ እየበረታ ያለ ፍርሃት ነጸብራቅ ነው ተባለ

ከምርጫ 97 ማግስት ጀምሮ በተቃዋሚ ፓርቲ አባላት ወይም በደጋፊነት በሚጠረጠሩት ላይ ዘርፈ ብዙ ጥቃቱን ያፋፋመው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ፤ የግንቦት 2002 ምርጫ እየተቃረበ ሲመጣ በዜጎች ላይ የሚያካሄደውን የመብት ረገጣ ወደ ከፋ ደረጃ እየወሰደው መሆኑን ከኢትዮጵያ የሚመጡ ዘገባዎች በማሳየት ላይ ናቸው።

ከጥቂት ሳምንታት በፊት በትግራይ ክልል የመድረክ ስብስብ አባል የሆነው የአረና ትግራይ ፓርቲ አባል እና የፓርላማ ምርጫ እጩ የነበሩት አቶ አረጋዊ ገብረዮሃንስ በገዛ ንግድ ቤታቸው ውስጥ በአሰቃቂ ሁኔታ መገደላቸው የሚታወስ ሲሆን፤ የሳቸው መገደል፣ በተለይም የአገዳደላቸው አሰቃቂነት፣ የአንድን ዜጋ የመኖር መብት ከመግፈፍ አልፎ ለሌሎችም እንደ ማስጠንቀቂያ መልክት የተደረገ መሆኑን ብዙ ተመልካቾች ተናግረዋል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በጋምቤላ ለፈጸመው ፍጅት አኟክ ኢትዮጵያውያን ሃላፊነቱን እንዲወስዱ በህዝቡ ላይ ከፍተኛ ጫና እየተደረገ መሆኑ ተዘገበ

እንደ ፈረንጆች አቆጣጠር በ2003 አመተ ምህረት የወያኔ ጦር በአባይ ጸሃዬ ዋና አዛዥነት በጋምቤላ በአኟክ ኢትዮጵያውያን ላይ ባደረሰው ፍጅት በመቶዎች የሚቆጠሩ መገደላቸውና፤ በሺዎች የሚቆጠሩም መፈናቀላቸው ይታወቃል። ይህ ወንጀልም የአለም አቀፍ ሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶችን ትኩረት መሳቡና መለስ ዜናዊን ጨምሮ እንደ አባይ ጸሃዬ እና ዶ/ር ገብረአብ በርናባስ ያሉት የወያኔ ባለስልጣናት በአለም አቀፍ ፍርድ ቤቶች ፊት ለፍርድ እንዲቀርቡ ተደጋጋሚ ጥሪዎች እየተደረጉ መሆኑን መዘገባችን ይታወሳል።

ጀኖሳይድ ዋች የተባለው እና የዘር ማጥፋት ወንጀሎችን እየተከታተለ የሚያጋልጠው ድርጅት መሪ ዶ/ር ግሬገሪ ስታንተን፥ በቅርቡ ከአሜሪካ ድምጽ ራድዮ የአማርኛ ዝግጅት ክፍል ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ፥ በወንጀሉ ውስጥ መለስን ጨምሮ የወያኔ ባለስልጣናት እጅ እንዳለበት የሚጠቁም መረጃ እንዳለ ተናግረዋል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## "ጀስቲስ ፎር ኦል ፕሪስን ፌሎውሺፕ" የተባለው ድርጅት መሪ ፓስተር ዳንኤል ገብረስላሴ በሙስና እንደተዘፈቀና ከወያኔ የደህነንት ቢሮ ጋር በሽርክና እንደሚሰራ ታወቀ

በየእስር ቤቶች ለእስረኞች መንፈሳዊ እና ቁሳዊ አገልግሎቶችን በማቅረብ ስራ እንደተሰማራ በድርጅቱ ድረ-ገጽ ላይ የሚገልጸው ፓስተር (ወይም መጋቢ) ዳንኤል ገብረስላሴ፣ በድርጅቱ ስራ ስም ከአለም አቀፍ የለጋሽ አገሮች ድርጅቶች ከሚሰበስበው ገንዘብ ውስጥ ከፍተኛ መጠን ያለው መመዝበሩ እንደተደረሰበት ለደህንነት ሲባል ስማቸው እንዳይጠቀስ የፈለጉ ታማኝ ምንጮች ለግንቦት 7 ድምጽ ባደረሱት መረጃ አስታውቀዋል።

መጋቢ ዳንኤል ገብረስላሴ የቅንጅት መሪዎችን ከወያኔ አገዛዝ ጋር አስታርቃለሁ በሚል ወደ ብሔራዊ የፖለቲካ መድረክ የመጣው እና በፕሮፌሰር ኤፍሬም ይስሃቅ የሚመራው የሽማግሌዎች ቡድን አባል እንደሆነ ይታወቃል። ግለሰቡ በቡድኑ ውስጥ ባደረገው ተሳትፎ እራሱን ለመለስ (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## የወያኔው አገዛዝ ያደረበትን የፍርሃት በሽታ በውሸት የኢኮኖሚ ዘገባዎች መሸፋፈኑን ቀጥሏል

የወያኔው የአዲስ አበባ የኢንቨስትሜንት ቢሮ 1.3 ሚሊዮን የስራ እድሎችን ፈጥሪያለሁ በማለት ሰሞኑን የተለመደ የቅጥፈት ፕሮፓጋንዳውን እየነዛ እንደሚገኝ የግንቦት ሰባት ዘጋቢ ከአዲስ አበባ በላከልን ሪፖርት ገልጿል። እንደ ዘጋቢያችን ገለፃ ግን የቢሮው ዘገባ ተአማኒነትን እንዳላተረፈ ለማወቅ ተችሏል።

ይህንን የአገዛዙን ፕሮፓጋንዳ አስመልክቶ ዘጋቢያችን ያነጋገራቸው የአዲስ አበባ ነዋሪዎች፥ ወያኔ በተለያዩ ጊዜያት የሚያወጣቸውን ቁጥሮች ብቻ ማጣቀስ ምናልባትም አገዛዙ ካለበት ውጥረት የተነሳ የተለያዩ ባለስልጣናቱ የሚናገሯቸውን ውሸቶች ማቀናጀት እንዳቃተው ያሳያል ብለዋል። አስተያየት ሰጪዎች፥ ወያኔ ራሱ የአዲስ አበባ ህዝብ 2.8 ሚሊዮን ብቻ ነው ማለቱን አስታውሰው፤ ይህንን እና በኢትዮጵያ ቤተሰቦች ውስጥ ያለውን መደጋገፍ ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ ከነዋሪው ወደ ግማሽ የሚጠጋው ስራ ቢኖረው አዲስ አበባ ውስጥ የሚራብ እና የሚለምን በታጣ ነበር ሲሉ ተሳልቀዋል።

በተያያዘ ዜና፥ በአገሪቱ ውስጥ ያለው የዋጋ ንረት እየተባባሰ እንደሄደ ሲሆን፣በፋሲካ በአል ወቅት እህልና ከብቶች ከዚህ በፊት ተሰምቶ በማይታወቅ ሁኔታ በመወደዳቸው፣ በብዙዎች ዘንድ አመት በአሉ ከወትሮው ቀዝቀዝ ብሎ እንዳለፈ ሪፖርተራችን ከአዲስ አበባ ዘግቧል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

# ርእሰ አንቀጽ



## መለስ ስታሊን ወይም ስታሊን መለስ

መለስ የስታሊንን ፍቅር በልቡ ይዞ ወደ ደደቢት በረሃ አቀና፤ እዚያም ታማኝ ደቀመዝሙሩ ሆነ። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ እስከዛሬ የስታሊንን እግር እየተከተለ ታማኝ ደቀመዝሙርነቱን እያስመሰከረ ነው።

"ከመምህሩ ደቀመዝሙሩ" እንዲሉ መለስ መምህሩን ስታሊንን የሚያስንቁ ተግባራትን እየፈፀመ ነው። ዛሬ ዛሬማ መለስ ዜናዊ ተብሎ መጠራቱ ቀርቶ መለስ ስታሊን ተብሎ ቢጠራ የተሻለ ነው። ከአቅም ማነስ በስተቀር በፍላጎትና በድርጊት ስታሊንን ልቆ በመሄዱም ስታሊን መለስ ብሎ መጥራትም ይቻላል። አንዳንዶቹን የመለስ ዜናዊ ስታሊናዊ ሥራዎችን ለአብነት እንጥቀስ።

1. ስታሊን ጨካኝና በቀለኛም እንደነበር ይታወቃል። ተቃዋሚዎቹን የብዙ ዓመታት እስራት እያስፈረደባቸው ወደ ሳይቤሪያ በግዞት በመላክ ይበቀላቸው ነበር። መለስም ከመምህሩ ያላነሰ ጨካኝና በቀለኛ ነው። ተቀዋሚዎቹን የብዙ ዓመታት በአንዳንዶቹም ላይ የእድሜ ልክ እስራት እያስፈረደ በቃሊቲና በበረሃዎች ባሉት እስር ቤቶቹ ውስጥ በጠባብ ጉሮኖ በማጎር ይበቀላቸዋል።
2. ስታሊን በሶቪየት ኮሚኒስት ፓርቲ ውስጥ የውይይት አጀንዳዎችን ራሱ እየቀረፀ ለሚፈልገው ውሳኔ ድምጽ የሚሰጡለትን አስቀድሞ አዘጋጅቶ ስብሰባ ይጀምር ነበር። መለስም አጀንዳ በመወሰን እና አጀንዳ በመጠምዘዝ "ድርጅታዊ አሠራር" በሚለው ሽር የፈለገውን ውሳኔ በስብሰባ የሚያስወስን መሠሪ ነው።
3. ስታሊን ዋና ዋና ተቋማትን እንደፈለጉ ለማሽከርከር በተቋማቱ ውስጥ ያሉትን ቁልፍ ሠራተኞችን እጅ ውስጥ ማስገባት ይገባል የሚል መርህ የነበረውና ተግባራዊም ያደረገ ሰው ነው። መለስም የመምህሩን አርዓያነት ተከትሎ የሃገሪቱን ተቋማትን በሙሉ በራሱ ሰዎች ያስያዘ ሰው ነው። መለስ መንግሥታዊ ያልሆኑት ባህላዊና የእምነት ተቋማትን ሳይቀር "በሰዎቹ" አማካይነት እየተቆጣጠረ ነው።
4. ስታሊን ራሱ ባይዋጋም የሶቪየት ሕዝቦችን ፀረ-ሂትለር ተጋድሎን ቀምቶ ሂትለርን ተዋግቼ አሸንፌዓለሁ እያለ ሲኩራራ የነበረ፤ ራሱ ግን ሂትለርን ሆኖ የተቀመጠ ሰው ነው። መለስ ራሱ በውጊያ እምብዛም ባይሳተፍም የሌሎችን ተጋድሎ ነጥቆ መንግሥቱ ኃይለማርያንም አሸነፍኩ ብሎ የሚኩራራ፤ ሆኖም ግን ራሱ ከመንግሥቱ ኃይለማርያም ብሶ የተገኘ ሰው ነው።
5. ስታሊን ብሄሮች እስከመገንጠል የሚደርስ የራሳቸውን እድል የመወሰን መብት አላቸው ቢልም ጥቃቅን የመብት ጥያቄ ያስነሱትን የዮክሬን፣ ሊቶንያ፣ ላትቪያ፣ ቮልጋ እና የራሱ የትውልድ ቦታ የጆርጂያ ሕዝብን ያስፈጀ አረመኔ ነው። መለስ ብሄሮች እስከ መገንጠል የሚደርስ የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት አላቸው ቢልም የመብት ጥያቄ ያስነሱ የኦሮሞ፣ የአማራ፣ የኦጋዴን፣ የአኙዋክ፣ የሲዳማ፣ የሸካና የአዲስ አበባ ሕዝብን ያስጨፈጨፈ አረመኔ ነው። ለገንዘብ ሲል የትውልድ አገሩ የትግራይን ሕዝብ በረሃብ ያስፈጀ ጨካኝ ነው።
6. ስታሊን በግብርና ኢንዱስትሪያላይዜሽን ሰበብ ብዙ ሚሊዮን ገበሬዎችን ከቀያቸው አፈናቅሎ በረሃብና በእርዛት እንዲያልቁ ያደረገ ሰው ነው። መለስ በኢንቬስትመንት ስም ብዙ ሺህ ጋሻዎችን ለባዕዳን በመስጠት ኢትዮጵያዊያን ገበሬዎች በረሃብ እንዲያልቁ እያደረገ ነው።
7. ስታሊን ላደረሰው ጭፍጨፋና የመብት አፈና ማካካሺያ አድርጎ ያቀርብ የነበረው "ሰላምና መረጋጋት" እና "ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት" ነበር። የኛው ጉድም እነዚህኑ መከራከሪያዎች ሌት ተቀን እየጋተን ነው።
8. ስታሊን በመንበረ ሥልጣኑ ለመደላደል እንዲያመቸው የቀድሞ የትግል አጋሮቹን ቡካሪን፣ ዚኔየቭየቭ፣ ትሮትስኪንና ካምኔቭን አባሮ በትግሉ ውስጥ ያልነበሩትን ሞሎቶቭን፣ ክርስቾቭን፣ ቡልጋኒን፣ ማሌንኮቭና ቤሪን በመተካት እሱ ብቻ የትግሉ አባት ሆኖ መታየት የቻለ ሰው ነበር። አዲሶቹ አገልጋዮቹ ስታሊንን የሰጣይን ያህል ይጠሉትም የዚያኑ ያህል ይፈሩትም እንደነበር ከሞተ በኋላ ራሳቸው ተናግረዋል። መለስም አብረው የታገሉትን የበረሃ ጓደኞቹን እነ ተወልደን፣ ሰለሞንን፣ አረጋሽን፣ ገብሩ፣ ፃድቃንና ስዬን ከገፈተራቸው ቆይቷል። አሁን ደግሞ ስዩም፣ ፀጋዬ፣ አባዲ፣ አርከበ፣ ቴዎድሮስ፣ አዲሱና ተፈራ ተደግሶላቸዋል። መለስ እንደ ሬድዋን ሃሰን፣ ኃይለማርያም ማሞ፣ መሃመድ ድሪር፣ ተሾመ ቶጋ፣ ሙክታር ከዲር፣ ድሪባ ኩማ እና ጁነዲን ሳዶ በመሳሰሉ እንደ ነቢይ በሚቆጥሩት ሰዎች እያጠረ ነው። በረከት ስምኦንም ሺመልስ ከማል በሚባል አዲስ ጥሩምባ ተተክቷል። አዲሶቹ አገልጋዮች መለስን በልባቸው ምን ያህል እንደሚጠሉት እድል ካገኙ ወደፊት እንደሚነግሩን እንጠብቃለን፤ በፍርሃት እንደሚርዱለት ግን ባይነግሩንም የምናውቀው ነው።

እርግጥ ነው በስታሊንና በመለስ መካከል ጉልህ ልዩነቶችም አሉ።

1. ስታሊን የኖረው ፋሺዝም ዓለምን ባመሰበት በሃያኛው ክፍለ ዘመን የመጀመሪያው አጋማሽ ላይ ሲሆን፤ መለስ ግን ፍትህና ዲሞክራሲ በገነኑበት በሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ነው።
2. ስታሊን ፋሺስት ቢሆንም አገር በመሸጥ አይታማም። መለስ ግን ዳሩን ጨርሶ መሃል አገሩን እያስረከበ ነው።
3. ስታሊን ብዙ ቆዳዎች፣ ብዙ ፊቶች እና ብዙ ምላሶች አልነበሩትም። ስታሊን ሁሌም ጨካኙ ስታሊን ነበር፤ አንዳችም አሳሳች ባህርይ አልነበረትም። መለስ ግን ብዙ ቆዳዎች፣ ብዙ ፊቶችና ብዙ ምላሶች ያሉት ባዕድ አውሬ ነው። በዚህም ምክንያት ሰዎችን በእጅጉ ያሳስታል።
4. ስታሊን በንዋይ ሙስና እምብዛም አይታማም። መለስ ግን ከረሃብተኛ ጉሮሮ እየነጠቀ ራሱን በሃብት ያንበሸበሸ ሰው ነው።

ውድ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ! ማን ሚኒሊክ ቤተመንግሥት ተቀምጦ በካርድህ ምረጠኝ እያለህ እንደሆነ ልብ ትላለህን? ማን በዲሞክራሲና ምርጫ ስም እየተገዘተ እንዳለ ትገነዘባለህን? እኛ "በቃ" ካልን ውለን አድረናል።

**ውርደት በቃን!**

## የዘረኛውና አምባገኑ መለስ ዜናዊ አገዛዝ በአሜሪካ . . . ከገጽ 1 የዞረ

ሽመልስ ከማል እነዚህ ሁለቱ ድርጅቶች የተያያዙት የኢትዮጵያን ምስል የማጥቆር ስራ ነው ሲልም ተችቷል። የወያኔው አገዛዝ በሰብአዊ መብት አያያዙ ላይ ከአለም አቀፍ ድርጅቶች ወቀሳና ሂስ ሲቀርብበት በኢትዮጵያ ላይ ጥቃት እንደተፈጸመ አድርጎ መቅረጽን የለመደው አሰራር ሲሆን፤ ተመሳሳይ ወቀሳና ሂስ በኢትዮጵያውያን ዜጎች ሲቀርብበት ደግሞ ጸረ-ሰላም፣ ጸረ-ልማት እና ጸረ-ብዙ ነገሮች እያለ በመወንጀል እንደሚያጠቃ ይታወቃል።

በተያያዘ ዜናም፥ አለም አቀፍ የጋዜጠኞች ፌዴሬሽን አርብ እለት ባወጣው መግለጫ፤ የመለስ አገዛዝ ቪኦኤን ለማፈን ያደረገውን ውሳኔ "ከአንድ መንግስት የማይጠበቅ" እና "ጠባብ" ሲል በጥብቅ አውግዞታል።

## የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በጋምቤላ ለፈጸመው . . . ከገጽ 1 የዞረ

የጋራ እንቅስቃሴ ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የተባለው ድርጅት ቅዳሜ ለት ባወጣው መግለጫ የዚህ ዜና መሰራጨት ውጥረት የፈጠረባቸው የወያኔ ባለስልጣናት የጋምቤላ ህዝብ ለተፈጠረው ፍጅት ሃላፊነቱን እንዲወስድ ለመጫን እርምጃዎችን መውሰድ መጀመራቸውን አስታውቋል። እንደ ድርጅቱ መግለጫ፥ በጋምቤላ የወያኔ ቅጥረኛ የሆነው የክልሉ ፕሬዘደንት ኦሞት ኦባንግ ኦሎም፥ የጋምቤላ ነዋሪዎች የወያኔ ጦር ለተደረገው ፍጅት ሃላፊነት እንደሌለበት፤ ይልቁንስ ጥፋተኞቹ ከ1991 አመተ ምህረት ጀምረው ደገኞችን ሲገድሉ የነበሩት አኟኮች ናቸው የሚል ጽሁፍ በሰፈረበት ፒቲሽን ላይ ፊርማቸውን እንዲያኖሩ እያስገደደ ነው።

ከዚህ በተጨማሪም፥ ኦሞት ኦባንግ የጋምቤላ ነዋሪዎች በአሜሪካ ድምጽ ራድዮ ላይ የቀረበውን ዘገባ በመቃወም እና የወያኔ ጦር ሃላፊነት የለበትም በማለት ሰልፍ እንዲወጡ ጫና ቢያደርግም፤ ህዝቡ አልታዘዝ ማለቱ ተዘግቧል።

## በህጋዊ እና ሰላማዊ ተቃዋሚ ፓርቲ አባላት . . . ከገጽ 1 የዞረ

ባለፈው ሳምንት ደግሞ የመድረክ ስብስብ አባል የሆነው የኦሮሞ ፌዴራላዊ ኮንግረስ ፓርቲ በመጪው ምርጫ እንዲወዳደሩ ያጫቸው አባላቶቹ ለእንግልት እና ለስቃይ እየተዳረጉ እንደሆነ መግለጫ መስጠቱን ዘግበናል። የዚሁ ስብስብ አባል የሆነው አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲም መጋቢት 18 ቀን ባወጣው "ጽናት" በሚባለው ጋዜጣው ላይ በጅማ ዞን አቶ ታሪኩ መኮንን በተባሉ የክልል ምክር ቤት እጩው ላይ የግድያ ሙከራ መደረጉን ዘግቧል። ጅማ ታይምስ የተባለው የዜና ድረ-ገጽ አቶ ታሪኩን አራት ጊዜ በጩቤ የወጓቸው የኦህዴድ ተቀጣሪዎች እንደሆኑ አርብ እለት ባወጣው ዘገባ አስታውቋል።

ከቀጥታ ድብደባ እና እስር በተጨማሪም በተቃዋሚ ፓርቲ አባላት ላይ፤ በተለይም የመንግስት ሰራተኛ በሆኑት ላይ፤ የተለያዩ እንግልቶች እና ጫናዎች እንደሚደረጉ ታውቋል።

ይህንን ጉዳይ በሚመለከት ያናገርናቸው አንድ የፖለቲካ ተንታኝ፥ እነዚህ ጥቃቶች ከሚፈጸሙባቸው ዋና ምክንያቶች ውስጥ አንዱ ኢትዮጵያውያንን ማስፈራራት ነው ብለዋል። የፖለቲካ ተንታኙ ጨምረውም፥ "አምባገነን መንግስታት ለህዝባቸው ማስጠንቀቂያ መልክቶች መላክ እንዳለባቸው የሚሰማቸው አለመረጋጋት ሲኖርባቸው እና ህዝቡ እንደማይደግፋቸው ስለሚያውቁ ነው" ካሉ በኋላ፤ "የመለስ አገዛዝ የተለያዩ ጫናዎች እንዳሉበት እና ከዛም የሚመነጨው ጥልቅ ፍርሃት እና በራስ ያለመተማመን ከጊዜ ወደጊዜ እየተባባሰ መሆኑን ያሳያል" ብለዋል።

## የወያኔው አምባገነን አገዛዝ በንጹሃን ዜጎች . . . ከገጽ 1 የዞረ

የወያኔን ድርጊት አስመልክቶ አስተያየታቸውን እንዲሰጡን የጠየቅናቸው በሃዋሳ ከተማ የሚገኙ ስማቸው እንዳይጠቀስ የጠየቁን ግለሰብ በሰጡን አስተያየት፤ የወያኔው አገዛዝ በየእለቱ አዳዲስ የግፍ ስራዎችን መፈጸሙ እየተለመደ እየመጣ ያለ እንደሚመስላቸው ከገለጹ በኋላ እንዲህ አይነቱን ግፍ በዝምታ እጃችንን አጣጥፈን በተመለከትን ቁጥር የጥፋቱ መጠንና ስፋት እየጨመረ መሄዱ አይቀሬ በመሆኑ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ከዚህ የበለጠ ጥፋትን ቁጭ ብሎ ከመጠባበቅ ይልቅ ለነጻነቱ መታገልና መዋጋት ብሎም የወያኔውን ግፈኛ አገዛዝ ለማስወገድ ቆርጦ ሊነሳ ይገባዋል ብለዋል።

በግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ የህዝብ ግንኙነትና
ቅስቀሳ ዘርፍ በሳምንት አንዴ የሚዘጋጅ ድርጅታዊ ልሳን

የፖስታሳጥን ቁጥር ፦ POBox: 4916
2003EX Haarlem, The Netherlands

## ውጭ ጉዳይ ሲገለጥ
## የሰፉም ነገር

**ክፍል 5 (የመጨረሻ ክፍል)**

በህዉሃት አገዛዝ ዘመን በዉጭ ጉዳይ መ/ቤት የሚፈፀመዉን በደልና ዝርፊያ በከፊል ለማሳየት ሰሞክር ይህ ነፍሰ ገዳይ ድርጅት(ህዉሃት) ከዚህ የሚማረዉ ነገር ይኖራል የሚል የዋህነት ኑሮኝ አይደለም። ይልቁንም ስለ እኩልነት፤ ስለ ፍትህ፤ ሰለ አንድነት፤ ስለ ዴሞክራሲ ድምፀፃቸዉን ከፍ አድርገዉ ሲሟገቱ በነበሩ የአገሪቷ ደግ ለጆች ላይ የሞት ፍርድ በ እነዝህ ነፍሰ ገዳዮች መፈረዱን ከሰማሁ በሁዋላ በራሴዉ አገርና በወንድሞቼ ላይ እንዲህ ዓይነት ፍፁም ኢፍትሃዊ የሆነ ዱርጊት መፈፀሙ ረፍት ሰለነሳኝ እኔም የማዉቀዉን የወያኔዎችን የረከሰ ምግባራቸዉን ልመስክር ብየ እንጂ። እነዚህ ወሮ በላዎች በግንቦት 7 መሪዎች ላይ የሞት ፍርድ ለመፍረድ የህግም ሆነ የሞራል መሰረት የላቸዉም ስለሆነም ሊፈረድባቸው የሚገባቸው ወያኔዎች እንጂ የግንቦት 7 መሪዎች አይደሉም።

በገዛ አገራችሁ ላይ ፍትህ ነግሦ ማየት የምትፈልጉ የቀደሞዉ የዉጭ ጉዳይ አባላትና በስደት ላይ የምትገኙ ውድ ኢትዮጵያዊያን በሙሉ የስደታችሁ ምንጭ ስዩም መስፍን እንደሚለዉ የአዉሮፓና የአሜሪካ በርገር ወይም ደግሞ የሆዳችሁ ነገር ከአገራችሁ በልጦባችሁ አይደለም።ይልቁንም በገዛ አገራችሁ ነፃነታችሁ በጨካኞችና በዘረኞች ስለተገፈፈ እንጂ። ይህ ሰዉ የመሆን ሚስጢራችሁን የገፈፈባችሁ ጨካኝ ቡድን አሁንም የብዙ ኢትዮጵያዊያንን መከራና ስቃይ እያበዛ አገራችንንም እያዋረደ ይገኛል። አሁን በያላችሁበት ሁናችሁ አገራችሁን ነፃ ለማዉጣት በሚደረገዉ ትግል ውስጥ የበኩላችሁን አስተዋፅኦ የምታበረክቱበት ወቅት ነዉ። አገራችሁ ተበታትና በህዝባችሁም ላይ የከፋ ችግር ደርሶ ከማየታችሁ በፊት በየአቅጣጫዉ የሚደረገዉን የነፃነት ትግል በእዉቀታችሁና በገንዘባችሁ እንድታግዙ ጥሪየን አቀርባለሁ።

የመጨረሻዉ መጨረሻ ደግሞ የትግራይ ነፃ አውጭዎች(ሕወሃቶች) ዴሞክራሲያዊ ስርዓት የሚጠይቃቸዉ ባህሪያትና ስነ-ምግባራት የሌሉት ክፉ ዘረኛ ድርጅት ነዉ።በዴሞክራሲ እሴቶች ላይ ያላገጠ በነፃነት ስም ሕዝብን ከፋፍሎ ሰብዓዊ መብትን የረገጠ በፍትህ ላይ የተሳለቀና የገዛ አገሩን ክብር ያዋረድ እንደ ህወሃት ያለ እኩይ ድርጅት ታይቶ አይታወቅም።ይህ ክፉ ጨካኝ ድርጅት በምንም መልኩ በሰላማዊ መንገድ በሚደረግ ትግል ስልጣን አይለቅም። ምክንያቱም ወንጀለኛ ድርጅት ነዉ። ይህን ወንጀለኛ ድርጅት ከህዝብ ጫንቃ ላይ ወደዚያ አሽቀንጥሮ ለመጣል ያለዉ መልካሙ መንገድ ለነፃነት ሲባል መተባበርና ጠላትን መፋለም ነዉ። ህወሃት ከውጭ ጠላት ያልተናነሰ በደል ፍፅሞብናል ስለዚህ ጠላት ነው እንጂ ሌላ የፖለቲካ ተፎካካሪ ሊሆነን አይችልም።

በመሆኑም በውጭ ያላችሁና ወያኔን በሚገባዉ ቋንቋ እናነጋግራለን ብላችሁ ትግል የጀመራችሁ ድርጅቶች (ግንቦት 7፤ ኦነግ፤ አርበኞች ግንባር፡ የኦጋዴን ነፃነት ግንባር እና ሌሎችም) ለላቀ ጥቅም ስትሉ ልዩነታችሁን አጥብባችሁ አንዳች አይነት ግንባር መፍጠር ጊዜ የሚሰጠዉ ተግባር አይደለም። ይህን ማድረግ ካልቻላችሁ ግን በግላችሁ ምንም ዓይነት ለውጥ ማምጣት የምትችሉ አይመስለኝም። አንዳች ዓይነት ግንባር ከፈጠራችሁ እኔን ብቻ ሳይሆን ሚሊየን ኢትዮጵያዊያንን ከጎናችሁ በማሰለፍ ይህ ነጻነትን የማያውቅ ነፃ አውጭ ድርጅት ወያኔን እንደ ኢሰፓ ብትንትኑን በማውጣት በፍርስራሹ ላይ ለሁላችንም የምትሆን ነፃ ኢትዮጵያን መፍጠር እንችላልን የሚል እምነት አለኝ። ስለዚህ የኢትዮጵያ የነፃነት፤ የእኩልነት፤የፍትህ እና የልማት ግንባር አሁኑኑ ይፈጠር ብየ ጥሪ ሳቀርብ በታላቅ ትህትና ነው።

ከሠላምታ ጋር
ወልዱ ተወልደ (የግንቦት ሰባት የመራጃ ምንጭ)
የዉጭ ጉዳይ ሰራተኛ።
ሠላም አንድነት እኩልነት የህግ የበላይነት እና እዉነተኛ ዲሞክራሲ ለኢትዮጵያችን ይሁን!!! ታህሳስ 21፣2002

በስደት ላይ ያሉት ዲፐሎማቶችና ሌሎች የውጭ ጉዳይ ሠራተኞች 81 የስም ዝርዝር፤

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1 | ዮሃንስ ጌንዳ | አምባሳደር | አቡጃ |
| 2 | ፍስሃ አዱኛ | አምባሳደር | ለንደን |
| 3 | ደ/ር ዋቅታሱ ነገሪ | አማካሪ | ሞስኮ |
| 4 | ሰይፈስላሴ ለማ | ሚኒስትር | ኒዮርክ |
| 5 | አልታየ አላሮ | አመካሪ | ቬየና |
| 6 | መስፍን እንዲሪያስ | አማካሪ | ዋሸንግተን ዲሲ |
| 7 | ብርሃኔ ገ/ህይወት | አማካሪ | ብራስልስ |
| 8 | ተሾመ ፍስሃ | አማካሪ | ቶኪዮ |
| 9 | ተስፋየ ደሳለኝ | 1ኛ ፀሃፊ | ዱባይ |
| 10 | እንዳልካቸዉ ሊበን | 1ኛ ፀሃፊ | ቤጂንግ |
| 11 | መስፍን ይማም | 1ኛ ፀሃፊ | ካይሮ |
| 12 | ፀጋየ ደመቀ | 1ኛ ፀሃፊ | ሄግ |
| 13 | ቢኒያም ከድር | 1ኛ ፀሃፊ | ኩዌት |
| 14 | ፀጋየ በቀለ | 1ኛ ፀሃፊ | ለንደን |
| 15 | ብርሃን መስቀል አበበ | 1ኛ ፀሃፊ | ኒዮርክ |
| 16 | ወገኔ አሰፋ | 1ኛ ፀሃፊ | ኒዮርክ |
| 17 | ብርሃኑ በየነ | 1ኛ ፀሃፊ | ሰነዐ |
| 18 | ጥላሁን ወ/ሰሞኦን | 1ኛ ፀሃፊ | ዋሺንግተን ዲሲ |
| 19 | ራሄል ኩመላ | 2ኛ ፀሃፊ | ኒዮርክ |
| 20 | ገነት አበበ | 2ኛ ፀሃፊ | ሄግ |
| 21 | ከንፈ ጌታቸዉ | 2ኛ ፀሃፊ | ቬየና |
| 22 | ጉልቴ ብርሃኑ | 2ኛ ፀሃፊ | ስቶኮልሆም |
| 23 | ጌታቸዉ ሓይሌ | 2ኛ ፀሃፊ | ቶኪዮ |
| 24 | ፀጋየ ኢዳኦ | 3ኛ ፀሃፊ | ዋሸንግተን ዲሲ |
| 25 | አሰቴር ሶሎሞን | 3ኛ ፀሃፊ | አቡጃ |
| 26 | ዘላለም ዳዊት | 3ኛ ፀሃፊ | ቤሩት |
| 27 | ፈጠነ ተፈራ | 3ኛ ፀሃፊ | ጂቡቲ |
| 28 | ዋጋየ ብርሃኑ | 3ኛ ፀሃፊ | ለንደን |
| 29 | አፖሎ እዳለ | አታሼ | አቢጃን |
| 30 | ታምራት ዳምጤ | አታሼ | ቤሩት |
| 31 | መጣአለም ስንሻዉ | አታሼ | ዳካር |
| 32 | ጌታቸዉ መኮንን | አታሼ | ጅዳ |
| 33 | ቡሩክ ከተማ | አታሼ | ሃርጌሳ |
| 34 | ፍሬህይወት በላቸዉ | ፀሃፊ | ኒዮርክ |
| 35 | ሄኖክ መንግስቱ | አታሼ | ዋናዉ መ/ቤት |
| 36 | ግርማ በላይነህ | አታሼ | ዋናዉ መ/ቤት |
| 37 | ደጀኔ ጭኮ | አታሼ | ዋሸንግተን ዲሲ |
| 38 | ምንያህል................ | ምሩቅ አታሼ | ዋናዉ መ/ቤት |
| 39 | ትዝታ ካሳ | አታሼ | ጅዳ |
| 40 | ታምራት አላዊ | አታሼ | ኒዮርክ |
| 41 | ትርስቲ ተካ | አታሼ | ብራስልስ |
| 42 | ሶሎሞን አሰፋ | አታሼ | ፕሪቶሪያ |
| 43 | ብርሃኑ ግዛቸዉ | አታሼ | ናይሮቢ |
| 44 | መሃመድ ሙስጠፋ | ተርጓሚ | ኩዌት |
| 45 | ሃና ካሳ | ፀሃፊ | ዋሸንግተን ዲሲ |
| 46 | መሰረት አክሊሉ | ፀሃፊ | ዋሸንግተን ዲሲ |
| 47 | ሃና ሐይሉ | ፀሃፊ | ኒዮርክ |
| 48 | ትግስት ለሜቻ | ፀሃፊ | ኒዮርክ |
| 49 | ሳባ ሙሉጌታ | ፀሃፊ | ቬየና |
| 50 | አዜብ ስለሺ | ፀሃፊ | ሄግ |
| 51 | ሉቧቧ እንዲሪስ | ፀሃፊ | ሄግ |
| 52 | ልዩወርቅ ደበበ | ፀሃፊ | ኩዌት |
| 53 | ተክለኪሮስ ተፈራ | የአምባሳደር ሾፌር | ኒዮርክ |
| 54 | ወሰን...... | የአምባሳደር ሾፌር | ኒዮርክ |
| 56 | መሃመድ ሴይድ | የአምባሳደር ሾፌር | ሄግ |
| 57 | ወንድወሰንተ/ማሪያም | ምግብ አብሳይ | ኩዌት |
| 58 | ታሪኳ...... | የፅዳት ሰራተኛ | ኩዌት |
| 59 | ሲሳይ ማሩ | 3ኛ ፀሃፊ | ዋናዉ መ/ቤት |
| 60 | ታደሰ ያዜ | ተ/2ኛ ፀሃፊ | ለንደን |
| 61 | በረከት ሳሙኤል | 3ኛ ፀሃፊ | ዋናዉ መ/ቤት |
| 62 | ሰላማዊት ዓሊ | 2ኛ ፀሃፊ | ቤጂንግ |
| 63 | ሙሉነህ ዮሃንስ | አታሼ | ዋናዉ መ/ቤት |
| 64 | ኤርሚያስ አላና | አታሼ | ዋናዉ መ/ቤት |
| 65 | ዳምጠዉ አሰፋ | 1ኛ ፀሃፊ | ዋናዉ መ/ቤት |
| 66 | ነብዩ ዳኜ | አማካሪ | ዋሸንግተን ዲሲ |
| 67 | ዳዊት ዘገየ | 2ኛ ፀሃፊ | ዋናዊ መ/ቤት |
| 68 | ታደለ አሰግዶም | 3ኛ ፀሃፊ | ጂቡቲ |
| 69 | እንዳልካቸዉ ታደለ | አታሼ | ደቡብ ኮሪያ |
| 70 | ቢኒያም.... | የአምባሳደር ሾፌር | ደቡብ አፍሪካ |
| 71 | ዮሃንስ ዳዲ | የአምባሳደር ሾፊር | ዋሺንግተን ዲሲ |
| 72 | ኤፍሬም ምህረታብ | | ለንደን |
| 73 | የምስራች ..... | 2ኛ ፀሃፊ | ኒዮርክ |
| 74 | እኩሉ ንዳ | አታሼ | ቴላቪቭ |
| 75 | ክብሩ ደመቀ | አታሼ | ቤጂንግ |
| 76 | አጥናፍሰገድ ዘለቀ | ተ/2ኛ ፀሃፊ | ቬየና |
| 77 | መላኩ....... | ምሩቅ አታሼ | ዋናዉ መ/ቤት |
| 78 | ዘውዱ ማሩታ | 1ኛ ፀሃፊ | ኦቶዋ |
| 79 | ፈቃዱ በላይነህ | ተ/2ኛ ፀሃፊ | ብራስልስ |
| 80 | ወርቅየ ብርየ | አማካሪ | ብራስልስ |
| 81 | ተስፋየ አባተ | አማካሪ | በርሊን |

## “ኢትዮጵያና የአፍሪካ ቀንድ” የተባለው ኮንፈረንስ በነገው እለት በዋሽንግተን ዲሲ እንደሚከፈት ተገለጸ

በበርካታ የኢትዮጵያውያንና አህጉር አቀፍ ሲቪክ ማህበረሰብ ድርጅቶች አዘጋጅነት ከሚያዚያ 1 እስከ 3፣ 2002 በዋሽንግተን ዲሲ በሚደርገው ስብሰባ ላይ በርካታ ኢትዮጵያውያን ምሁራን እና የሌላ አገር ዜጎች ምሁራን እንደሚገኙ ለማወቅ ተችሏል። ኮንፈረንሱ በሚቆይባቸው ሶስት ቀናት በአስተዳደር፣ ሰላም፣ ደህንነት እና ልማት ዙሪያ በበርካታ ርእሶች ላይ ንግግሮች እና የጥናት ጽሁፎች እንደሚቀርቡ ከወጣው ፕሮግራም (የጊዜ ቀመር?) ለመረዳት ችለናል።

ኮንፈረንሱ አርሊንገተን ቨርጂኒያ በሚገኘው ደብል ትሪ ሆቴል የሚካሄድ ሲሆን፤ በስፍራው ለመገኘት ላልቻሉ ሰዎች ethiov.com በተባለ ድረ-ገጽ ላይ በቪዲዮ በቀጥታ እንደሚተላለፍ ለማወቅ ችለናል። በኮንፈረንሱ ላይ ተጨማሪ መረጃን ለማግኘት advocacyforethiopia.org የሚባለውን ድረ-ገጽ መጎብኘት እንደሚቻል ለአድማጮቻችን ልንገልጽ እንወዳለን።

## “ጀስቲስ ፎር ኦል ፕሪስን ፌሎውሺፕ” የተባለው . . . ከገጽ 1 የዞረ

ዜናዊ አገዛዝ መሳሪያነት ማዋሉ ከተለያዩ ሰዎች ወቀሳን ሲቀሰቅስ እንደቆየም ይታወቃል። በቅርብ ጊዜ ደግሞ በወያኔ ቁጥጥር ስር በሚገኘው የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ላይ በመቅረብ የወያኔ አገዛዝ ፍትሃዊ እንደሆነና እስር ቤቶቹም ከአፍሪካ አንደኛ እንደሆኑ መናገሩ በብዙ ኢትዮጵያውያን ዘንድ ቁጣን ቀስቅሷል።

እንደ ምንጮቻችን ገለፃ፥ ከዚህ ቀደም ፕሪዝን ፌሎውሺፕ በመባል በሚታወቀው በመጋቢ ዳንኤል ድርጅት ውስጥ ገንዘብ እየተሰረቀ መሆኑ የተደረሰበት በቅርቡ በድርጅቱ ላይ በተካሄደ ኦዲት ወይም የሂሳብ ማወራረድ ስራ ወቅት ነው። መጋቢ ዳንኤል የሂሳብ ውርርዱ እንዳይሰራ አክሮ ተቃውሞ እንደነበር የገለጹት ምንጮቻችን፣ በያገሮቻቸው ተጠያቂነት ያለባቸው ለጋሽ ድርጅቶች አማራጭ እንደሌለ እንደነገሩት አክለዋል። ለጋሽ ድርጅቶቹ የሂሳብ ማወራረዱን ስራ ለማድረግ የተነሳሱትም ለድርጅቱ ቅርብ ከሆኑ ግለሰቦች በደረሳቸው ጥቆማ መሰረት እንደሆነ ታውቋል።

ከመጋቢ ዳንኤል ድርጅት የተመዘበረው ገንዘብ የት ውሎ እንደሆን ለማወቅ የግንቦት 7 ድምጽ ባደረገው ተጨማሪ ጥረት፣ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ምንጮችን ደህንነት ለመጠበቅ ስማቸውን ወይም ከድርጅቱ ጋር ያላቸውን ግንኙነት ለመግለጽ ወደማንችለው ተጨማሪ ምንጮች መርቶናል። ከፕሪዝን ፌሎውሺፕ ጋር ቅርበት ያላቸው ምንጮች፥ በድርጅቱ ንብረት ክፍል ውስጥ በተራ ደሞዝ ይሰራ የነበረውን የመጋቢ ዳንኤልን ወንድም ሃብት እንደ አንድ ምሳሌ ይጠቅሳሉ። የመጋቢ ዳንኤል ገብረስላሴ ወንድም ከየት እንዳመጣው በማይታወቅ ገንዘብ የብዙ ጭነት መኪናዎች እና የሁለት ኮብራ ላንድክሩዘሮች ባለቤት መሆኑና፤ ጭነት መኪናዎቹን ለግንባታ ድርጅቶች፣ ላንድክሩዘሮቹን ደግሞ ለጎብኚዎች እያከራየ እንደሚጠቀም ለማወቅ ተችሏል።

በተጨማሪም፥ መጋቢ ዳንኤል ከፍተኛ መጠን ያለው ንዋይ አፈሳለሁ በሚል ብርሃነ አዴሎ በተባለው የወያኔ ባለስልጣን እርዳታ በከፋ ዞን ትልቅ የእርሻ መሬት መውሰዱን ምንጮቻችን ገልጸዋል።

በድርጅቱ ውስጥ ያላቸውን ስራ የለቀቁ ብዙ ግለሰቦች ከሚሰጡት ዋና ዋና ምክንያቶች ውስጥ አንዱ፥ ወደ መስሪያ ቤቱ ሲገቡ መጋቢ ወይም ፓስተር የሚል ማእረግ ስላለው የእግዚአብሔር ሰው ነው የሚል ግምት ይዘው እንደሆነ፤ ነገር ግን በድርጅቱ ውስጥ ያለውን ምዝበራ ሲመለከቱ ከመጸየፋቸው የተነሳ መቀጠል ባለመቻላቸው አነደሆነ የደረሰን መረጃ ያመለክታል።

በመጋቢ ዳንኤል ድርጅት ላይ የተደረገው የሂሳብ ማወራረድ ስራ ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብ መመዝበሩን ካጋለጠ በኋላ የተወሰኑ ለጋሽ ድርጅቶች ለድርጅቱ ገንዘብ መስጠት ማቆማቸውን ለማወቅ ችለናል። በዚህ ያልተደሰተው መጋቢ ዳንኤልም ከመለስ ዜናዊ አገዛዝ ጋር ያለውን ቅርበት እየጠቀሰ ጫና ሊፈጥርባቸው እየሞከረ እንዳለም ለመረዳት ችለናል።

የመጋቢ ዳንኤል ድርጅት መቶ በመቶ ገቢውን የሚያገኘው ከውጭ ለጋሾች ሲሆን፣ ወያኔ አዲስ ባወጣው መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ህግ መሰረት፥ እንደ ውጭ አገር ድርጅት የሚቆጠር እና ከመብት ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ መስራት የማይችል ነው። ከዚህ ህግ ጋር በተያያዘ ብዙ ቁጥር ያላቸው መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በራቸውን ለመዝጋት እንደተገደዱ ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸው ምንጮች አስታውቀውናል። መጋቢ ዳንኤል ግን እንደ ወያኔ ባለስልጣናት እና ድርጅቶች ይህ ህግ እንደማይመለከተው እና በጉዳዩ ላይም ከአገዛዙ ጋር ልዩ ስምምነት እንዳለው እንደሚናገር ምንጮቻችን ገልጸዋል።

በርግጥም ይህ ድርጅት ለመለስ ዜናዊ አገዛዝ ያለውን ጥቅም ግልጽ አድርጎ በሚያሳይ ሁኔታ፥ የድርጅቱ የውስጥ አዋቂ ከሆኑ ሌላ ምንጭ የተገኘ መረጃ እንደሚገልጸው፥ የመጋቢ ዳንኤል ድርጅት ከወያኔ የደህንነት ቢሮ ጋር በሽርክና ይሰራል። ከ1997ቱ ምርጫ በኋላ በአስር ሺሆች የሚቆጠሩ ዜጎች በየጦር ካምፖች ሲታጎሩ፣ የወያኔ የደህንነት ቢሮ በነዚህ አዳዲስ እስር ቤቶች ሰላዮችን ያስቀምጥ ነበር። በዚህ ወቅት በቃሊቲ እስር ቤት ዞን አራት (**ወደ ላይ ይቀጥላል**)

## የአሜሪካ ድምጽ ራድዮ የአሜሪካ መንግስት አፈና ሲካሄድ ዝም ብሎ አይመለከትም አለ

እሮብ አለት ባወጣውና “ዝምታ በኢትዮጵያ ወርቅ አይደለም” የሚል ርእስ ባለው ድረ-ገጹ፤ የአሜሪካን መንግስት አመለካከት እንደሚያንጸባርቅ በድረ-ገጹ ላይ የሚገልጸው የአሜሪካ ድምጽ ራዲዮ (ወይም ቪኦኤ)፤ የአሜሪካ መንግስት በኢትዮጵያ አፈና ሲካሄድ እያየ ዝም ለማለት አይችልም ብሏል።

ብሔራዊ ምርጫው በተቃረበ ቁጥር መለስ ዜናዊ ሚዲያዎችንም የሚተላለፈውን መልክትም ለመቆጣጠር ቆርጦ የተነሳ ይመስላል ያለው ቪኦኤ፤ የአማርኛ ፕሮግራም ስርጭቱን ያፈነው መለስ ዜናዊ የድርጅቱ ድረ-ገጽም ኢትዮጵያ ውስጥ እንዳይታይ ማገዱን አውግዟል። የአማርኛ ራድዮ ስርጭቱ ወደ ኢትዮጵያ እንዳይተላለፍ ከታገደበት በኋላ የሳተላይት ስርጭት የጀመረው ቪኦኤ፣ ሌላ ዘዴዎችንም እያፈላለገ መሆኑን ገልጿል።

ቪኦኤ፥ ሁሉም ተወዳዳሪዎች በነፃነት መሳተፍ ካልቻሉና የፖለቲካ ዜናዎች ከታፈኑ አንድ ምርጫ ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ሊካሄድ አይችልም ብሏል።

## የወይዘሪት ብርትኳን ሚደቅሳ የጤና ሁኔታ . . . ከገጽ 1 የዞረ

በተያያዘ ዜና ፓስተር ዳንኤል ገብረስላሴ በሙስና መዘፈቁን በቅርቡ በድርጅቱ ላይ የተደረገ ኦዲት ወይም ሂሳብ የማወራረድ ስራ ማጋለጡን ስማቸው እንዳይጠቀስ የፈለጉ ምንጮች ለግንቦት 7 ድምጽ ገልጸዋል። የእግዚአብሔር አገልጋይ ነኝ የሚለው ይህ ግለሰብ እንደ ወያኔ ላለ ኢ-ፍትሃዊ አገዛዝ መጠቀሚያነት እራሱን ማቅረቡ ብዙዎችን ግራ ሲያጋባና ሲያሳዝን መቆየቱ ይታወቃል። የፓስተሩን ሙስና በተለመለከተ መረጃ ከላኩልን ግለሰቦች ውስጥ አንዱ፣ የዚህ መረጃ መገለጥ ግራ መጋባቱን እና ብዥታውን ያጠራዋል ብለው እንደሚያምኑ ነግረውናል።

## የወያኔው አገዛዝ ያደረበትን የፍርሃት በሽታ . . . ከገጽ 1 የዞረ

ሪፖርተራችን በመጨመርም በመንግስት መስሪያ ቤቶች ያለፈው ወር ደሞዝ የተከፈለው በአብዛኛው በአስር ብር ኖቶች እንደሆነ፤ እና የሃምሳ እና የመቶ ብር ኖቶች እጥረት እንዳለ ዘግቧል። ይህ ምን ማለት እንደሆነ የጠየቅናቸው አንድ የኢኮኖሚ ባለሙያ፥ የዋጋ ንረት በከፋባቸው አገሮች ትናንሽ ኖቶች ዋጋ እያጡ ይሄዱና ሰዎች የሚገበያዩት በብዛት በትላልቅ ኖቶች ይሆናል፤ የትላልቅ ኖቶች እጥረት የተፈጠረውም በዚህ ምክንያት ይሆናል ብለዋል። ባለሙያው የዚምባብዌ መንግስት ባገሩ ባለው ከፍተኛ የዋጋ ንረት ምክንያት እስከ ሚሊዮኖች የሚደርሱ ዋጋ ያላቸውን ኖቶች ለማተም መገደዱን አስታውሰው፤ በኢትዮጵያ ያለው የዋጋ ንረት በዚሁ ከቀጠለ፣ አገዛዙ የአምስት መቶ እና ከዛም በላይ ብር ዋጋ ያላቸውን ኖቶች ለማተም ሊገደድ እንደሚችል ገልጸዋል።

## “ጀስቲስ ፎር ኦል ፕሪስን ፌሎውሺፕ” የተባለው . . . ከገጽ 4 የቀጠለ

ውስጥ ሰራተኛ የነበረ ኤርምያስ የተባለ ወያኔ ወደ ዴዴሳ የጦር ካምፕ በጊዜያዊነት ሲላክ የአገዛዙ ሰራተኛ እንደሆነ ሆኖ አይደለም የሄደው። ኤርምያስ በወቅቱ በዴዴሳው አዲስ የዜጎች ማጎሪያ የስለላ ተልእኮውን ሲፈጽም የነበረው የመጋቢ ዳንኤል ገብረስላሴ ድርጅት ሰራተኛ ሆኖ ነበር። በወቅቱም ይህ ድርጅት ዳጎስ ያለ ደሞዝና የለት አበል ይከፍለው እንደነበር ምንጫችን አክለዋል።

መጋቢ ዳንኤል ገብረስላሴ እንደ ሽማግሌዎች ቡድን አባል በአንድ ወገን የእግዚአብሔር አገልጋይ ነኝ እያለ ለመለስ ዜናዊ መሳሪያነት እራሱን አሳልፎ መስጠቱ ብዙዎችን፣ በተለይም ባለው የአገልግሎት ማእረግ ምክያት የሚያከብሩትን፣ ሲያሳዝን መቆየቱ ይታወቃል። በዚህ ሪፖርት የቀረቡትን መረጃዎች ከላኩልን ግለሰቦች አንዱም፥ ይህ መረጃ ስለገለሰቡ ያለውን ግራ መጋባት እና ብዥታ ያጠራዋል ብለው እንደሚያምኑ ገልጸዋል።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**
**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**
**በ 7530 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ** እና **በ 9610 KHZ በ 31 ሜትር ባንድ** ላይ የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

**ውድ አንባቢዎቻችን**
ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዮን ክፍላችን ዎይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ
ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን g7radio@ginbot7.org ወይም በስልክ ቁጥር 0044- 203-286- 9661